# ፍኖተ ዲሞክራሲ የራዲዮ ስርጭት መደመጥ ያለበት ሰባት ምክንያቶች

ዜናነህ በቀለ

ፍኖተ ራዲዮ ስርጭቱን የጀመረው በአገር ቤት ኢሕአፓ ይንቀሳቀስ ከነበረበት ነጻ  መሬት ሲሆን እኔ ስርጭቱን ካርቱም ሆኜ በጥሞና እከታተል ነበር። አዳማጭ ጠፋ እንጅ ዛሬ በኢትዮጵያችን ላይ የምናየው ክፉ ነገር ሁሉ በወያኔዎች እንደሚፈጸም ትክክለኛ ግምት ያኔ ሰጥቶ ነበር። አሁን  ደግሞ ከውጭ ወደ አገር ቤት በሚያሰራጨው የሳቴላይት ራዲዮ ከገባንበት የወያኔ ሰለባ እንዴት ልንወጣ እንደምንችል ሳይታክት ሕዝቡን በማስተምርና በማነሳሳት ላይ ይገኛል። ይህ የራዲዮ ስርጭት ለምን በሁላችንም መደመጥ እንዳለበት ሰባት ምክንያቶች እነሆ።

አንደኛ

ፍኖተ ራዲዮ መሰረታዊ ዓላማው **የኢትዮጵያ ብሔራዊ ስሜትን** መዳበርና ማሰራጨት ነው። የበርካታ ብሔረሰቦቻችንን ህልውና እንዲጠበቅ እየሞገተ እነዚህ የተበራከቱ ብሔረሰቦች ሊልቁና ሊከበሩ የሚችሉት ኢትዮጵያዊ የሆነውን ብሔራዊ ስሜትን ከፍ ሲያደርግ ብቻ ስለመሆኑ  ድሮም ሆነ ዛሬ በጥሞን አስደምጦናል። እያስደመጠንም ነው። ነገም መሰል ተግባሩን ይቀጥልበታል። በወያኔ የረከሰው ሰንደቃላማችን የብሄራዊ ስሜታችን መለዮ ስለመሆኑ የሚሰማ ጆሮ ካላቸው የሚታዘቡት ዕውነታ ነው።

ሁለተኛ

ፍኖተ የስርጭቱ መሰረቱ **በዕውነት ላይ የተመሰረቱ ዜናዎችን** ማሰማት ነው። ፍኖተ ራዲዮ ስርጭቱ እውነትነት ያላቸውን ዜናዎች እንደወረደ ያቀርባቸዋል። ርካሽ ዝናን በመፈለግ በሬ ወለደ ዜና አያቀርብም። ፍኖተ አማራጭ ዕውነት(alternative fact) የተባለ ቅዥት አያውቅም። የፍኖተ ራዲዮ ስርጭት በዕውነትና እውነት ላይ የተመሰረተ ነው።

ሶስተኛ

**የፍኖተ ራዲዮ አስተማሪ ነው።** አስተማሪ ዕውቀትን ያስተምራል። ፍኖተ ራዲዮም ሕብረተሰቡ በተለያዩ ዕውቀቶች ማለትም በፓለቲካው፣ በኢኮኖሚው፣ በማሕበራዊው . . .  ወዘተ ማወቅ የሚገባውን ሁሉ ግልጽና አቀራረብ ርቱዕ በሆነ መንገድ ያቀርባል። ሕብረተሰቡ ወያኔንና መሰሎቹን እንዴት መቃወምና ማጥቃት እንደሚችል ያስተምራል። ማን የአገርና የሕዝብ ጠላት እንደሆን ቁልጭ አድርጎ ለሕብረተሰቡ ዕውቀትን ይመግባል። ስለ ዲሞክራሲና ሰብዓዊ መብቶች ምንነነት በጥራት ያስተምራል። ዲሞክራሲና ሰብዓዊ መብቱ እንዲከበርለት የሚፈልግ ድርጅት ከጸረ ዲሞክራሲና ስብዓዊ መብትን ከሚጥሱ መንግስታት ጋር እንዳያብሩ ያስተምራል።

አራተኛ

**ፍኖተ ሕዝቡን አደራጅ ነው።** የወያኔ አፈናና ግድያ ሕዝቡ አንገቱን እንዳያስደፋው የጎብዝ አለቃ እየመረጠ እንዲደራጅና ጠላትን እንዲፋለም አስተምሯል። ሕዝቡም በተማረው መንገድ **የጎበዝ አለቃውን** ሲያመች በግልጽ ሳያመች በሕቡዕ እየሰየም የወያኔን ምድር ቀውጢ በማድረግ ላይ መሆኑን እያየነው ነው። ድርጅቶችም ወያኔን ለመደምሰስ ሊከተሉት የሚገባቸውን መንገድና ዘድዴዎች ካካበተው የዘመናት ተመክሮ በመሞርኮዝ ያካፋላቸዋል። ያስተምራቸዋል።

አምስተኛት

የፍኖተ ራዲዮ ስርጭት **ሙያተኞች ግልጋሎት የሚሰጡት ያለክፍያ በነጻ ነው።** ይህ ደግሞ ከማናቸውም የዜና ስርጭት ሚዲያዎች ፍኖተ ራዲዮን ልዩ ያደርገዋል። ሙያተኞቹን ግልጋሎት እንዲሰጡ የሚያደርጋቸው ለአገርና ለሕዝብ ያላቸው ልዩ ፍቅር መሆኑ በገሃድ የሚታይ ነው። የሬዲዮ ስርጭቱን በገንዘብ እንዲረዱ ከአገርና ወገን ጠላቶች ጋር አይሞዳመደም። ስርጭቱ በኢትዮጵያውያንና በአይበገሬ መንፈሰ ጠንካራ አባላቱ ድጋፍ ነው።

ስድስተኛ

ፍኖተ ራዲዮ ስርጭት **በረጅም ዘመናት ተመክሮ የዳበረ** ታሪክ አለው። ስርጭቱን የጀመረው በደርጉ ዘመን ኢሕአፓ ነጻ ባወጣው መሬት ላይ ሲሆን አሁን ደግሞ ከዲያስፖራ ወደ አገር ቤት ስርጭቱን ተያይዞታል። ስርጭቱ ዕውን የሚሆነው በአባላቱና በደጋፊ ኢትዮጵያውያን ወገኑ ነው። ከባዕዳን ያውም የኢትዮጵያን ሕልውና ከማይፈልጉ የውጭ አገሮች ሰማይ ወደ ምድር ምድርም ወደ ሰማይ ይገለባበጣሉ እንጅ ዕርዳታቸውን አይፈልግም።

ሰባተኛ

**ፍኖተ ራዲዮ ስርጭቱ ውጤታማ ነው።** ማለትም ስርጭቱ በአገር ቤት በብዙሃኑ ይደመጣል። ሕዝቡም ያደመጠውን እንደ አስፈላጊነቱ ተግባራዊ ያደርጋል። በተለይ በሕዝቡ መሃል ዘረኛነትን ለማሰራጨት የሚሞክሩ ሃይሎችን ማለትም ወያኔንና የወያኔን አንቀጽ 39 አቀንቃኞችን ሙከራ ውድቅ እንዲሆንና ተቀባይነት እንዲያጣ ዘውትር ይጥራል። ወያኔ በቀደደው የዘረኛነት ቦይ ሊኄዙ የፈለጉትን ተገቢ ያለመሆኑን በማስረዳት ከቦዩ ወጥተው ከነበሩበት ኢንዲሆኑና እትዮጵያውያን መድረክ እንዲመደቡ አድርጓል። ስርጭቱ ተጭሆ ያለውጤት የሚተን ሳይሆን በአዳማጮች መሃል አገር ወዳድነትንና ከሁሉም በላይ ኢትዮጵያዊነት ማየሉን አስተምሮ ሕዝባዊ ፍቅርን አግኝቷል።

# እና . . .

ፍኖተ ራዲዮ ስርጭት ምንኛ አስፈላጊ መሳሪያችን ስለመሆኑ ስባት ሳይሆን በርካታ ምክንያቶችን ማቅረብ ይቻላል። ፍኖተ ራዲዮ ጥሩ ስራ እየሰራ ስለመሆኑና በርካታ ኢትዮጵያውያን እንደሚያዳምጡት ከመግለጽ ባሻገር ለሕዝብ ነጻነት የሚያስብ ሁሉ ፍኖተ የበለጠ እንዲጠናከር በገንዘብ ማገዝ ይጠበቅብናል። የስርጭት ሞገዱ ከወያኔ አፈና እንዲያመለልጥ ጠንካራና ሃያል ስርጭት እንዲሆን ከሁሉም በላይ የገንዘብ ድጉማ ማድረግ ይጠበቅብናል። አመርቂ ስርጭቱን ለማዳመጥና በርካታ ትምህርት ለመቅሰም የፍኖተ ራዲዮ ስርጭትን እንዲያዳምጡ ኢትዮጵያውያኑ ሁሉ ጆሮ እንዲሰጡት ማሳሰቡ ተገቢ ነው።። ማዳመጥ ብቻ ሳይሆን በስርጭቱ ሁሉ ተሳትፎ በማድረግ ለማሳደግ የሚሰጡትን ምክር ሁሉ ፍኖተ ራዲዮን ያጠናክራል።